የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፸፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፲፪

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th year number 71
ADDIS ABABA July 28th , 2020

<u>ማውጫ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ፳፻፲፫ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፸፩/፪ሺ፲፪
ገጽ .................. ሺ፮፻፶፱

**CONTENTS**

Addis Ababa City Administration 2020/21 G.C. Fiscal Year Budget proclamation 71/2020
Page ........................................... 1659

## አዋጅ ቁጥር ፸፩/፪ሺ፲፪

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር</u>

## <u>የበጀት አዋጅ</u>

ለ፪ሺ፲፫ የበጀት ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት አጽድቆ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወቅት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ለ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፩/፪ሺ፱ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

## Proclamation No 71/2020

## <u>BUDGET PROCLAMATION OF ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION</u>

WHERE AS, it has become necessary to approve and disburse on time the budgetary appropriation for under taking by the Addis Ababa City Administration during the 2020/21 G.C.

NOW THEREFORE, in accordance with Article 14(1) (B) of the Addis Ababa City Administration Revised charter proclamation No. 361/2003 and the Addis Ababa city administration financial administration proclamation number 51/2017 article 17 the Council of Addis Ababa City Administration proclaimed as follow;

*ያንዱ ዋጋ*
**Unit Price**

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፶፭ሺ፮፻፺፰
Addis Negari Gazeta P.O.Box 55698

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የ፪ሺ፲፫ በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበጀት አዋጅ ቁጥር ፸፩/፳፻፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. የተፈቀደ በጀት

ከሐምሌ ፩ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ፳፻፲፫ በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኘው ገቢ እና ከሌላ የገቢ ምንጭ የሚገኝ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፣

**ሀ/ ለማዕከል መ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ፩. ለመደበኛ ወጪዎች ብር | 11,435,494,141.00 |
| ፪. ለካፒታል ወጪዎች ብር | 27,090,953,728.00 |
| ፫. ለመጠባበቂያ በጀት ብር | 3,000,000,000.00 |
| **የከተማ ድምር** | 41,526,447,869.00 |

**ለ /ለክፍለ ከተሞች**

| | |
|---|---|
| ፩.ለመደበኛ ወጪዎች ብር | 16,131440,678.00 |
| ፪.ለካፒታል ወጪዎች ብር | 3,692,732,868.00 |
| **የክፍለ ከተሞች ድምር** | 19,824,173,546.00 |
| **ጠቅላላ ድምር ብር** | 61,350,621,415.00 |

### ፫. ጥቅም ላይ ያልዋለ ጥሬ ገንዘብ

ሀ. በባለፉት ዓመታት ተሰብስቦ ስራ ላይ ያልዋለ ጥሬ ገንዘብ በዚህ በጀት ዓዋጅ እንደ አንድ የገቢ ምንጭ የቀረበው በ2013 በጀት ዓመት ስራ ላይ እንዲውል ተፈቅዷል፣

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Administration 2020/21 G.C Budget Proclamation No 71/2020"

### 2. Allocated Budget

The Addis Ababa City Administration Budget is here by appropriated for the fiscal year commencing on July 09, 2020 G.C and ending on July 08, 2021 G.C from Addis Ababa City Administration revenues and other funds, for the purposes and services set forth in the schedule here to;

**A/ City Sector Bureaus**

| | |
|---|---|
| 1.For Recurrent Expenditure Birr | 11,435,494,141.00 |
| 2.For Capital Expenditure Birr | 27,090,953,728.00 |
| 3. For Contingency Birr | 3,000,000,000.00 |
| **Total** | **41,526,447,869.00** |

**B/ Sub Cities**

| | |
|---|---|
| 1.Recurrent Expenditure Birr | 16,131,440,678.00 |
| 2.Capital Expenditure Birr | 3,692,732,868.00 |
| **Sub Cities Total** | **19,824,173,546.00** |
| **GrandTotalBirr** | **61,350,621,415.00** |

### 3. Un Used liquid Cash

a. Revenue collected in the previous years but not yet used, is hereby Authorized for 2020/21 Budget year to put in to use.

ለ. ከላይ የተቀመጠው አጠቃላይ በጀት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ ሆኖ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

## ክፍል ሁለት
## የበጀት አስተዳደር

### ፬. የከተማ አስተዳደር አካላት ሥልጣን

፩. የክፍለ ከተማ የፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ ለክፍለ ከተማው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደለትን በጀት በሚጠይቅበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

፪. ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለየመስሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ እንደ አግባብነቱ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ወይም የክፍለ ከተማው ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ ወይም ለክፍለከተማው ከተፈቀደው በጀት እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል፤

፫. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩት ሆስፒታሎች፣ጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፤ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩንቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣የቲያትር ቤቶች፣ የትምህርትና ስልጠና ጥራት፤ሙያ ብቃትና ምዘና ባለስልጣን፤ የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን ጠቅላላ የበጀት መጠን ሳያልፍ ከዘመኑ በጀት

b. The City Government of Addis Ababa is hereby authorized to disburse the total amount mentioned above through this proclamation.

## PART TWO
## BUDGET ADMINSTRATION

### 4. POWER OF THE CITY ADMINISTRATION ORGANS

1. The head of Finance Bureau is here by authorized and directed, up on the Request of the head of the Finance Office of a Sub City to disburse out of the City Administration revenues and other funds the amounts appropriated here in for the purposes and services off a Sub City.

2. The head of Finance Bureau, or head of Finance Office of a Sub City is here by authorized upon the request of the heads of the concerned public bodies, to disburse out of the city Administrations revenues and other funds or out of a Sub City's appropriate budget the amount appropriates here in for purposes and services of this respective bodies.

3. Hospitals, Health Centers, Schools, TVET Colleges, Kotobe Metropolitan University, Water & Sewerage Authority, Theater houses, Educational and Training Quality, Occupational Competency and Assessment Authority, Gulelle Botanic Garden are allowed to retain and expend

ዓመት ገቢያቸው በፋይናንስ ህግ መሰረት ወጪ እያደረጉ ቀጥታ በጥቅም ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ ኘሮግራም፣ የሥራ ክፍል፣ የሂሣብ መደብ መዝግበው በመያዝ በየወሩ ለፋይናንስ ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለካፒታልም ሆነ ለመደበኛ ተጨማሪ ሥራዎች ከውጭ ብድር እንዲሁም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙትን ብድር ወይም እርዳታ በሥራ ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ አርዕስት፣ በንዑስ አርዕስት ኘሮግራም፣ በኘሮጀክት ሥር መዝግበው በተጨማሪ በጀት በመያዝ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለፋይናንስ ቢሮ ሪ□ርት ማድረግ አለባቸው።

## ፭. የበጀት ዝውውር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፶፩/፳፻፱ አንቀጽ ፳፪ እና ፳፯ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ የበጀት ዝውውር በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፤

፩. በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

<u>**የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ**</u>:-

ሀ/ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ መደበኛ በጀትን በሚመለከቱ የወጪ መደቦች ውስጥ የበጀት ዝውውር ለማድረግ፣

ለ/ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በጀትን ከአንድ ካፒታል ኘሮጀክት ወደ ሌላ የካፒታል ኘሮጀክት ለማዛወር፣

within the limit of their budgetary appropriations receipts from the current fiscal year and shall record the amount under its program, department, and codes and shall report monthly to Finance Bureau

4. Public bodies are hereby authorized to record on their appropriate budgetary head, sub head, project, or program, as the case may be, and undertake all acts necessary for the Utilization of any additional loan or aid in kind and/or cash obtained from foreign or local source for carrying out capital project or recurrent programs, and report to the Finance Bureau before one month from the end of the budget year.

## 5. <u>BUDGET TRANSFER</u>

Without prejudice to the provisions of Article 22 and 27 of the Addis Ababa City Administration Financial Administration proclamation No 51/2017 budget transfer shall be executed as follows:

1) **Budget Transfers within Public Bodies**

<u>The Finance Bureau Head may within a Public Body</u>:-

a. transfer funds within items of expenditure of the recurrent Budget;

b. transfer budget from one capital project to another within a Public Body ;

ሐ/ አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለተፈቃደ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት የካፒታል ፕጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ከተፈቀደ የካፒታል ፕሮጀክት ለማዘዋወር፤

መ/ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ሥር ያሉ መስሪያ ቤቶች ሲዋሃዱ ወይም ሲነጣጠሉ በጀቱን ከአንድ ወደሌላው ለማዘዋር ስልጣን ተሰጥቶታል፤

፪. የፋይናንስ የቢሮ ኃላፊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስልጣን በውክልና አግባብ ላለው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል፤

**፫. በከተማው ማዕከልና በክፍለ ከተማዎች ወይም በመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር**

፩ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት የማይጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ በጀቱን ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለማዘዋወር ይችላል፡፡

፪. የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት እንዲዘዋወር ሊፈቅድ ይችላል፤

ሀ/ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያጋጠመን የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል በበጀት ዓመቱ ለሌላ

c. Transfer the budget approved for capital expenditure of the Public Body to finance pending obligations of a project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year;

d. Transfer the budget when organs under a Public Body merge or split.

2 The Finance Bureau Head may delegate the appropriate head of public body to exercise the power vested in him under sub- article 1 of this Article

**3 Budget Transfers between Public Bodies & Sub Cities**

1. The Finance Bureau Head may transfer a recurrent budget from one Public Body to the other if it is ascertained that the Public Body to which the budget is appropriated cannot wholly utilize its budget,

2. The Finance Bureau Head may authorize the transfer of funds from the capital budget of one Public Body to the capital budget of another Public Body under the following conditions

(a) Where a deficiency in one Public Body's capital budget can be met by an offsetting transfer from another Public Body's capital

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ ያልዋለን የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል ለተፈቀደ የካፒታል ፕሮጀክት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለተፈቀደ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት ፕሮጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፡፡

## ፬. ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው ተራፊ በጀት መኖሩን ሲያረጋግጥ ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማው ወይም ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ የክፍለ ከተማ የሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል።

## ፭. በጀት ዝውውር መደረጉን ስለማሳወቅ

በዚህ አዋጅ በጀትን የማዛወር ሥልጣን የተሰጣቸው አካላትና ኃላፊዎች የበጀት ዝውውሩን እንደፈቀዱ ወዲያውኑ እንደ አግባብነታቸው ለቢሮው ወይም ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

አዲስ አበባ
ሐምሌ ቀን ፪ሺ፲፪

ኢ/ር ታከለ ኡማ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ

budget approved for that fiscal year provided the capital budget receiving additional funds is a previously approved capital budget.

(b) Where a budget is requested to finance pending obligations of a project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year.

## 4. Budget Transfers City to Sub cities

The Finance Bureau Head, on the conformation of any unused budget, may transfer a budget from a center Public Body to the sub city or from Sub City to Center public Body. With the same manner the sub city Finance Office Head may transfer budgets from a sub city to a center Public Body.

## 5. NOTIFICATION OF BUDGET TRANSFER

According to this proclamation, the authorized officials and heads of public bodies for transferring budget shall immediately notify in writing to the Finance Bureau or Office as the case may be.

Done at Addis Ababa
July 28, 2020

Takele Uma (Eng.)
Deputy Mayor of Addis Ababa City Government

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ፳፻፲፫ በጀት ዓመት የገቢና የወጪ አሸፋፈን

### 1. የከተማው ገቢ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. የአገር ውስጥ ገቢ | ጠቅላላ ብር | |
| ታክስ ገቢ | 42,495,543,865.21 | |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 5,195,430,663.11 | |
| የማዘጋጃ ቤት ነክ አገልግሎቶች ገቢ | 6,884,117,151.68 | |
| የመንገድ ፈንድ | 150,000,000.00 | |
| የአገር ውስጥ ገቢ ድምር | | **54,725,091,680.00** |
| ከባለፉት ዓመታት ተራፊ ጥሬ ገንዘብ | | **5,000,000,000.00** |
| ለ. የውጭ እርዳታና ብድር | | |
| የውጭ ዕርዳታ | 29,412,521.00 | |
| የውጭ ብድር | 1,596,120,214.00 | |
| የውጭ እርዳታና ብድር ድምር | | **1,625,532,735.00** |
| **የከተማው ጠቅላላ ገቢ ድምር** | | **61,350,624,415.00** |

### 2. የከተማው ወጪ

| | |
|---|---|
| ሀ. መደበኛ ወጪ | ብር |
| የመደበኛ ወጪ ድምር | 27,566,934,819.00 |
| ለ. የካፒታል ወጪ | |
| የካፒታል ወጪ ድምር | **30**,783,686,596.00 |
| ሐ. የመጠባበቂያ ወጪ | |
| የመጠባበበቂያ ድምር | 3,000,000,000.00 |
| **ጠቅላላ የወጪ ድምር** | **61,350,621,415.00** |

## ADDIS ABABA CITY Administration 2020/21 BUDGET EXPENDITURE COVERAGE

### 1. REVENUE

| City Administration Revenue Birr | Total Birr |
|---|---|
| A. Domestic Revenue | |
| Tax revenue | 42,495,543,865.21 |
| Non-tax revenue | 5,195,430,663.11 |
| Municipal service revenue | 6,884,114,151.68 |
| Road funds | 150,000,000.00 |
| **Total Domestic Revenue** | **54,725,091,680.00** |
| **Liquid Cash From previous years** | **5,000,000,000.00** |
| B. External Assistance and Loan | |
| External Assistance | 29,412,521.00 |
| External Loan | 1,596,120,214.00 |
| **External Assistance and Loan Total** | 1,625,532,735.00 |
| **Total Revenue** | **61,350,621,415.00** |

### 2. EXPENDITURE

| | |
|---|---|
| **A. Recurrent Expenditure** | |
| **Total Recurrent Expenditure** | 27,566,934,819.00 |
| **Capital Expenditure** | |
| **Total Capital Expenditure Total** | **30,783,686,596.00** |
| **C. Contingency** | |
| **Total Contingency** | 3,000,000,000.00 |
| **Total Expenditure** | **61,350,621,415.00** |

## 3. ለክፍለ ከተሞች የተመደበ በጀት

| | መደበኛ ወጪ | ካፒታል ወጪ | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|
| **የክፍለ ከተሞች ጠቅላላ ድምር** | **16,131,440,678** | **3,692,732,868** | **19,824,173,546** |
| አራዳ ክፍለ ከተማ | 1,360,553,294 | 190,931,147 | 1,551,484,441 |
| አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ | 1,319,381,795 | 173,536,009 | 1,492,917,804 |
| ልደታ ክፍለ ከተማ | 1,097,143,148 | 176,501,165 | 1,273,644,313 |
| ቂርቆስ ክፍለ ከተማ | 1,282,912,743 | 136,994,719 | 1,419,907,462 |
| የካ ክፍለ ከተማ | 2,025,697,625 | 481,834,629 | 2,507,532,254 |
| ቦሌ ክፍለ ከተማ | 1,830,006,395 | 740,483,943 | 2,570,490,338 |
| አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ | 1,926,053,393 | 431,838,587 | 2,357,891,980 |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ | 1,732,383,984 | 549,403,144 | 2,281,787,128 |
| ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ | 2,235,161,586 | 603,993,643 | 2,839,155,229 |
| ጉለሌ ክፍለ ከተማ | 1,322,146,715 | 207,215,882 | 1,529,362,597 |

## 3. Budget for Sub-Cities

| | Recurrent Expenditure | Capital Expenditure | Total |
|---|---|---|---|
| **Sub-Cities** Total | **16,131,440,678** | **3,692,732,868** | **19,824,173,546** |
| Arada | 1,360,553,294 | 190,931,147 | 1,551,484,441 |
| Addis Ketema | 1,319,381,795 | 173,536,009 | 1,492,917,804 |
| Lideta | 1,097,143,148 | 176,501,165 | 1,273,644,313 |
| Kirkos | 1,282,912,743 | 136,994,719 | 1,419,907,462 |
| Yeka | 2,025,697,625 | 481,834,629 | 2,507,532,254 |
| Bole | 1,830,006,395 | 740,483,943 | 2,570,490,338 |
| Akaki Kaliti | 1,926,053,393 | 431,838,587 | 2,357,891,980 |
| Nefas Silk Lafto | 1,732,383,984 | 549,403,144 | 2,281,787,128 |
| Kolfe Keranio | 2,235,161,586 | 603,993,643 | 2,839,155,229 |
| Gulelle | 1,322,146,715 | 207,215,882 | 1,529,362,597 |